# ላ ስ ተ ዋ ው ቃ ች ሁ

ከሥርጉተ ሥላሴ
መስከረም 2001 ዓ. ም.

መክሊት አብ ትባላለች። የድህረ ገፃችን የልጆች ክፍል አንባቢ ናት::

መክሊት የስምንት ዓመት ሴት ልጅ ስትሆን ውጭ ሀገር ተወልዳ አድጋ ነገር ግን ለሃይማኖቷ ባላት ልዩ ፍቅርና በወላጆቿ ድጋፍ ልክ አገር ቤት ተወልደው ከአደጉት ልጆች እኩል የአማርኛ ቋንቋ  አጣርታ ታነባለች:: አትኮላተፍም:: መክሊት በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከአሉ ዘማሪ ታዳጊ ልጆች አንዷ ናት:: በሌላ በኩል ደግሞ በስዊዘርላንድ “ የተስፋ ድምጽ” የሬድዮ ፕሮግራም ከሀገር ውጭ ካሉት የሬዲዮ ፕሮግራሞች ሁሉ “ተስፋ” በሚለው የልጆች የዜግነት ትምህርት መምሪያ የመጀመሪያዋ አንባቢና አቅራቢ ታዳጊ ልጅ ናት::

አድማጮቿ፣ አድናቂዎቿ  ለሬዲዮ ፕሮግራም አስተያየት ሲሰጡ እያለቀሱ ነው:: ስለምን በፍጥረተ ነገሯ ለዩት ያለች ታዳጊ ልጅ በመሆኗ:: እኔ የእርሷ አማካሪዋ፣ አሰልጣኟ፣ መምህሯ፣ ጽሑፍ አቅራቢዋ እንደመሆኔ መጠን ያላትን ኃላፊነት የመወጣት ብቃትዋን በሚመለከት ትንሽ ማለት እፈልጋለሁ::

1. እርምት ፈጥና ትቀበላለች የተሰጠውንም እርምት ተግባራዊ ታደርጋለች::
2. በቀጠርኳት ሰዓት ትጠብቀኛለች፣ አገኛታለሁ::
3. ኃላፊነት ይሰማታል / ቢያማት እንኳ ትሰራለች / ::
4. ድምፅዋን ለመግራት የማደርገውን ጥረት ፍሬያማ አድርጋልኛለች:: ይህም የውስጥ ፍላጎቷን በማሳዘዝ እረገድ ብቃቷን ያሳያል::
5. አትሰለችም:: ምክንያቱም አየር ላይ ከመቅረቧ በፊት ተደጋጋሚ ጊዜ እያነበበች እርማት ይደረግላታል:: ግን ሳትሰለች “ ልቀጥል? “ “ ደግሜ ላንብበው? “ በማለት በትህትና በመጠዬቅ ሙያውን ለማሻሻል እና በጥራት ለማቅረብ ልዩ ጥረት ታደርጋለች::
6. ሁሉን ነገር እንዳለ አትቀበልም:: ትጠይቃለች:: ባላመነችበት ነገር ትከራከራለች :: ታሳምንማለች:: (በምሰጣት ስክሪፕት ላይ  በቂ የሆነ አስተያዬት ትሰጥበታለች::)
7. ጥሩ አድማጭ ናት::
8. እርምትም ትሰጣለች አንድ ጊዜ ያነሳችውን ብቻ ልግለጥ:: “ ቋሚ “ የሚል ከፅሑፉ ላይ አስገብቸበት ስለነበር ግን ገብቶሻል “ ቋሚ “ ማለት ስል ጠዬኳት:- እውነት ተናጋሪ ስለሆነች “አልገባኝም” አለች:: ቋሚ ማለት <u>ሁል ጊዜ</u>  አዘውትረሽ የምታደርጊው ማለት ነው:: ለምሳሌ ማታ ማታ መተኛት አልኳት:: ቀልጠፍ ብላ  ታዲያ ሥርጉተ <u>ቋሚ</u> ይውጣና <u>ሁልጊዜ</u> ለምን አንለውም “ አለችኝ:: እጅግ ነው የገረመኝ:: አውነትሽን ነው:: እንዳለ ይባል አልኳት::
9. አልገቡኝም የምትላቸውን በደንብ ይሰረዝ ስላት ግድ የለም አላነበውም ትልና አየር ላይ የቀረውን ወይንም የተውነውን ሀረግ ታነባለች ብዬ ስጠብቅ ዘላ አስተካክላ ስሜቱን ሳትሰባብር የማንበብ ችሎታዋ ደግሞ ይህች ልጅ ለዚህ ዘመን ይሆን የተፈጠረችው ? ብዬ እራሴን እንድጠይቅ አድርጎኛል::

እንደ መክሊት አብ የተለያየ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላችሁ ብዙ ልጆች በየቦታው እንደ አላችሁ ስለምናውቅ ወደፊት በዚህ መድረክ እንደምንገናኝ ተስፋ እናደርጋለን። ለግንኙነታችን ደግሞ በአድራሻችን እንድትጽፉልንና ለተሳትፎአችሁ መድረኩን በማመቻቸት በኩል አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ የፀጋዬ ድኅረ ገፅ የሎሬት ተስፋ የልጆች አምድ ክፍል አዘጋጆች ቃል ይገባሉ።

## መ ል ካ ም  አ ዲ ስ  ዓ መ ት ::

## እ  ን  ቁ  ጣ  ጣ  ሽ ! ! !